# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የወንጀለኛው መንግስት መደናበርና
## የሕዝባዊ ትግል መስፋፋት

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር፡ 2
ህዳር—ታህሳስ 1965

# የመንግስቱን ጋዜጠ በናገለበጥ

## እምባ ጨፋሪ አንዱ በርባሪ

የመንግስቱ የፕሮፖጋንዳ መሳሪያዎች ህዝቡን ለማደናገር የሚጠቀሙበት ዘዴ ቢዘቅ ቢቆ ማለቂያ የለውም:: ዛሬ እዚህ ላይ ለማውጣት የምንፈልገው በአቶ ፓውሎስ ኞኞ እየተሰናዳ ስለሚቀርበው 'የጥያቄና መልስ' አምድ ነው:: ይስ እንግዲህ በወዲህ በጋዜጣው በኩል የአደናጋሪው 'የመምህር አበራራው' እምባያ መሆኑ ነው:: አቶ ፓውሎስ ኞኞ በዚህ አምዳቸው 'ተጠየቁሁ' እያሉ 'የማይመልሱት' ጉዳይ ከሰማይ በታች የሚገኝ አይመስለንም:: አንዱ 'ሁለትና ሁለት ስንት ነው' ብሎ ይጠይቃቸዋል:: አቶ ፓውሎስ 'አራት ነው' ብለው እቅጩን ይመልሳሉ:: አንዷ 'ባለንጀራዬ በአገብስ እየሰደበች አስቸገረችኝ' ብላ ታማርራለች አቶ ፓውሎስ 'ተው አትሳደቡ' ብለው አረጋዊ ምክራቸውን ይለግሳሉ:: አንዱ 'እህ ኻለ' ብሎ ይጠይቃቸዋል:: አቶ ፓውሎስ 'አለና' ብለው ይመልሳሉ::

ታዲያ ይህ ሁሉ ባልከፋ ነበር:: ጋዜጣ ሲባል ለአንድ የደህንነት ጉጉት ላደረበትና ለተጨቆነ ህዝብ የደህንነቱንና የነጻነቱን ጥርጊያ ጉዳና ማስተማሪያ መሳሪያ ሆኖ ባይታየን ኖሮ እንዲህ አይነቱን ድርቅ ያለ 'ኮምክና' እንደምንም በቀን ባሳለፍነው ነበር::

ግን አያስቅንም:: አባቶቻችን ሲተርቱ 'እምባ ጨፋሪ አንዱ በርባሪ' ያሉት ጉዳይ ነው:: የአቶ ፓውሎስ እምባ መልሶች እምባ ማደናገሪያዎች ናቸው:: በየቀኑ ከሚቀርበው እ

ብ ነጻነትን ተገፍፎ:ከብሩን አዋርዶ:በውጭ ወራሪዎች ተ
ረግጦ:ከባርነት ጋር ተደብሎ:ታሪኩንና ኑሮውን አጉድፎ
ይዞ ወደ::ለምን::ማን ህዝብ እንደተሸበረ::ማን ህዝ
ብ እንደተፈታ::እነሙሶሎኒ ትላንት የፈጸሙበት ተመሳሳይ
ወንጀል የነጻነትን ትግል መች ገታው::እነሱንስ ከማይቀ
ረው ጥፋት መች አዳናቸው::ዛሬስ ቢሆን ፋሽስቶች በአን
ጎላና በሞዛምቢክ የሚፈጽሙት ተመሳሳይ ግፍ እነዚህ ህዝ
ቦች ወደነጻነታቸው የሚያደርጉትን ተመሳሳይ ትግል መች ገ
ታው::ቀራጡ የቪየትናም ህዝብ ወደነጻነት:
ወደአንድነቱና ወደድል የሚያደርገውን ግስጋሴ መች አቆመ

የኢትዮጵያ ህዝብ በያለበት የሚያደርገው ትግል
በሚገባ ተቀናብሮ በአንድ ሃይልና በአንድ አላማ ሲዳብር
የከሃዲዎችንና የኢምፔሪያሊስቶችን ሴራ አከሽፎ በትግሉ
ነጻነትን ይጎናጸፋል::ትላንት የሙሶሎኒ የመርዝ ጢስ ነጻ
ነትን አላፈነውም::ዛሬም የአሜሪካ ፋሽስቶች መርዝ ለነጻ
ነት የሚያደርገውን ትግል በምንም አይነት አይፈታውም::

ህዝባችን እንደገና የመርዝ ጢስ አይፈልግም

የሀገራችን ውበት ሲረገፍ ዝም አንበል

ፋሽስትአሜሪካ ሀገራችንን ለቆ ይውጣ

የኢትዮጵያ ከሃዲዎች ይውደሙ